# የአዊ ብሔረሰብ ባህላዊ ህግ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ይድነቃቸው ከበደ

መስፍን እሸቱ

የትናየት ደሳለኝ

1 የአዊ ብሔረሰብ ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት የሚሰጠውን አገልግሎት እና ተቀባይነት ከግምት በማስገባት የባህላዊ ሕጎችንና የባህላዊ ተቋማትን አሰራር በተመለከተ ዝርዝር ሕግ አለመውጣቱ በአፈፃጸም ረገድ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ በመሆኑም የሕግ አውጪው አካል ዝርዝር ህግን በማውጣት ይህን ችግር ሊፈታው ይገባል፡፡

2 ከዚህ ቀደምም ሆነ ወደ ፊት በባህላዊ ህግ ዙሪያ ለተደረጉት እና ለሚደረጉት ጥናቶች የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተለይም በዚህ በኩል የትኞቹ የባህላዊ ሕጎች እና ቷቋማት ናቸው ጠቃሚዎቹ? ሕገ መንግስቱ ካስቀመጣቸው መሰረታዊ መርሆዎች ጋር ተጣጥመው መሄድ የሚችሉት እንዴት ነው? ባህላዊው ሕግና መደበኛው የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓት እንዴት ሊመጋገቡ ይችላሉ? ወዘተ… የሚሉትን በስፋት መርምሮ ጠቃሚ የሚባሉትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከአካባቢ ባህላዊ የግጭት መፍቺያ ተቋማት ውስጥ ግጭቶችን በመፍታት የጎላ ልምድ ያላቸውን የአገር ሽማግሌዎች በተለያዩ የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ መደበኛው እና ባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት የሚመጋገቡበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

3 ግጭቶችን አስቀድሞ የመከላከል እና ሲከቱም በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሚሆነው የማህበረሰብ ተሳትፎ ሲኖር ነው፡፡ የማህበረሰቡ ተሣትፎ መኖር የአዊ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት አይነተኛ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት ግጭቶችን እንዴት መከላከል እና መቆጣጠር ብሎም መፍታት እንደሚቻል በግጭት ፈቺነት ከሚሳተፉት የአገር ሽማግሌዎች ምክር የሚያገኙበትን አደረጃጀት፣ መዋቅር እና አሰራር መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

4 እያንዳንዱ ግጭት የራሱ ባህርይና መንስዔ እንዳለው በመረዳት ከግጭቱ ዓይነትና ከህዝቡ ባህል አንፃር እየታየ ከአካባቢው ባህላዊ ግጭት መፍቻ ተቋማት ጋር በህብረት በመስራት ግጭቶችን የመፍታት ልምድ ይበልጥ የሚዳብርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

1 የአዊ ብሔረሰብ ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓትን ማህበረሰቡ እስከ አሁን ድረስ ለግጭት መፍቻ እየተጠቀመው ያለ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን እየተዳከመ የመጣ በመሆኑ መንግስትና የሚመለከተው አካል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡